በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

እንኳን ለዐቢይ ጾም ሰባተኛ ሳምንት "ኒቆዲሞስ" በሰላም አደረሳችሁ!!!

የዚህ ሳምንት ስያሜ ኒቆዲሞስ ይባላል። ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን ሲሆን የአይሁድ አለቃ፣ የእስራኤል መምህርና የኦሪት ምሁር /ዮሐ. 3÷1፤ 3÷10፤ 7÷51/ ነበር ። ኒቆዲሞስ ፈሪሳውያንን ፈርቶ የአይሁድ አለቃም ስለሆነ አይሁድ ከሚቃወሙት መሲህ ጋር ከታየ እርሱንም ሊቃወሙት ስለሚችሉ በሌሊት እንጂ በመዓልት፤ በጨለማ እንጂ በብርሃን ወደመሲሁ መሄድ አልቻለም። ቢሆንም ይህ ፍርሃት የጌታን ትምህርት ከመማር አላገደውም፤ በሌሊት ብርሃን ወደ ሆነው ክርስቶስ መጣ። ከዚያም በኋላ በዮሐ. 7÷51 ላይ እንደምናገኘው በድፍረት ስለጌታ ባይመሰክርም አይሁድ በክፋት ተነሳስተው ጌታን ሳይመረምሩ እንዳይፈርዱበት ግን አሳስቧቸዋል።

<u>ምስባክ</u> ፡

"ሐወጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ፤
አመከርከኒ ወኢተረክበ ዓመጻ በላዕሌየ፤
ከመ ኢይንብብ አፉየ ግብረ ዕጓለ እመ ሕያው። "
መዝ. ፲፮፥ ፫-፬

" ልቤን ፈተንኸው በሌሊትም ጐበኘኸኝ፤
ፈተንኸኝ፥ ምንም አላገኘህብኝም።
የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው"
መዝ. 17፥ 3-4

በዚህ ሰንበት የሚነበበው ወንጌል የዮሐንስ ወንጌል 3÷ 1-11 ሲሆን የኒቆዲሞስንም ታሪክ የምናገኘው በዚህ

የመጽሐፍ ክፍል ነው። "ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። እርሱም በሌሊት ወደ ጌታችን

ኢየሱስ መጥቶ እንዲህ አለው..."

ኒቆዲሞስ ትንቢተ ነቢያትን የሚያውቅ ፈሪሳዊ እንዲሁም ከጌታ ዘንድ በማታ በመመላለስ የተማረ ቢሆንም ለመረዳት ያስቸገረው አንድ የጌታ ትምህርት ግን ነበር፤ ይህም **"የሰው ልጅ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልገዋል"** የሚለው ትምህርት ነበር። ጌታንም "ሰው ካደገ በኋላ እንዴት ወደ እናቱ ማሕጸን ተመልሶ ሊወለድ ይችላል?" በማለት ጠይቆታል። ጌታም **"ከውሃና ከመንፈስ ትወለዱ ዘንድ አለችሁ"** በማለት በጥምቀት የሰው ልጅ ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን አስተምሮታል። /ዮሐ. 3÷ 5/ አንድ ሰው በሥጋ ከወላጆቹ ሳይወለድ በዚህ ዓለም መኖር እንደማይችል ሁሉ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ያልተወለደም በመንፈሳዊው ዓለም መኖር አይችልምና። **<u>ከኒቆዲሞስ ምን እንማር?</u>**

1. **አትጎቶ ርእስን /ራስን ዝቅ ማድረግን/**፡- የምናውቅ ቢመስለንም ገና ብዙ የማናውቀው አለና በትህትና ከታላላቆቻችን ሥቨቨር ሆነን ልንማር ይገባል። ኒቆዲሞስ ፈሪሳዊ መምህር ነኝ ብሎ በልቡ ስለተፈጠረበት ጥያቄ ከጌታው ከመማር ወደኋላ አላለምና፤ ለሚታበዩ አዋቂ ነን ባዮች ማስተማርያ ሆኗል
2. **ትግሃ ሌሊትን /በሌሊት መትጋትን/፡-** ቀን አይሁድን በመፍራት ባይማርም በሌሊት ግን ፈጽሞ ሳይታክት ይመላለስ ነበር፤ በዚህም ለምሥጢረ-ጥምቀት መገለጥ ምክንያት ሆነ
3. **እስከ መጨረሻ መጽናት፡-** ጌታን ካገኘባት ሰዓት ጀምሮ በሌሊት የተመላለሰው ኒቆዲሞስ እስከመጨረሻው በጌታው በማመኑ በዕለተ ዓርብ የጌታውን ሥጋ ከዮሴፍ ዘአርማትያስ ጋር ከመስቀል አውርዶ በአዲስ መቃብር እያመሰገነ ለመቅበር በቅቷል። ጌታም ምን ብለው ሊገንዙት እንደሚገባ የነገራቸውን ምስጋና "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት....." ቤተ-ክርስቲያንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ጌታዋን ስታመሰግንበት ትኖራለች።

እንግዲህ እኛ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ከኒቆዲሞስ ሕይወት እነዚህንና ሌሎች ብዙ ቁምነገሮችን እንማራለን። የኒቆዲሞስ በሌሊት ገስግሶ መምጣት ለምሥጢረ ጥምቀት ትምህርት መገለጥ ምክንያት እንደሆነ ሁሉ በቅዳሴው፣ በኪዳኑ፣ በሰዓታቱና በማኅሌቱ መገኘትና መሳተፍ ረቂቅ የሆነው ሰማያዊ ምሥጢር ፍንትው ብሎ አንዲገለጥልን ያደርጋልና በምሥጢራት በመሳተፍ ራስን ዝቅ በማድረግ ለታላቅ ክብር እንድንበቃ የጌታ መልካም ፈቃድ ይሁንልን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!

የቅዱስ ጳውሎስ ሕክምና ግቢ ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፳፭፣ ፳፻፲፭ ዓ.ም